## መመሪያ ቁጥር 227/2013

**ያገለገሉ የቶነር ካርትሬጆችን አወጋገድ እና ተሞልሰው በመንግሥት መ/ቤቶች ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ፣**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 78 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "በመንግሥት መ/ቤቶች ያገለገሉ የቶነር ካርትሬጆች አወጋገድ እና ተሞልሰው በመንግሥት መ/ቤቶች ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 227/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል፡፡

2. **የመመሪያው ዓላማ**

የዚህ መመሪያ ዓላማ፡-

1. የመንግሥት መ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸው ለፕሪንተር፣ ለፎቶ ኮፒ ማሽን እና ለፋክስ መሣሪያዎች ወ.ዘ.ተ አገልግሎት የሚሰጥ ቀለም የሚይዙ የቶነር ካርትሬጆች አገልግሎታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ሊከተሉት የሚገባውን የአወጋገድ ስርዓት ፣
2. በድጋሚ የቶነር ቀለም የተሞሉ ካርትሬጆች ግዥ ለሚፈፀም የሚቻልበትን ሁኔታ መወሰን ይሆናል፣

3. **አወጋገድ**

የመንግሥት መ/ቤቶች ለስራቸው የተጠቀሙባቸውና አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የቶነር ካርትሬጆችን ሰብስበው በማከማቸት ለአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት በደረሰኝ ያለክፍያ ያስረክባሉ፡፡

4. **ስለፈቃድ አሠጣጥ**

1. በአንቀጽ 3 መሠረት ከመንግሥት መ/ቤቶች ያገለገሉ ካርትሬጆችን የሚሰበስቡ አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ከፌዴራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ፈቃድ የተሰጣቸው ብቻ ናቸው፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተሰጠ የቶነር ማሰባሰብ ፈቃድ የፌዴራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ በሚወስነው ጊዜ ማሳደስ ይኖርበታል፡፡

5. **የብቃት ማረጋገጫ**

በድጋሚ የተሞሉ ወይም የቶነር ቀለም በድጋሚ የተሞሉ ወይም የተገጣጠሙ የቶነር ካርትሬጆችን ለመንግሥት መ/ቤቶች በሽያጭ ለማቅረብ ፍላጎት ያላቸው አቅራቢዎች የሚያቀርቧቸው የቶነር ካርትሬጆች በኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው መሆን አለባቸው፡፡

6. <u>**የጥራት ደረጃ**</u>

በአንቀጽ 5 ከተመለከተው የብቃት ማረጋገጫ በተጨማሪ ለሽያጭ የሚቀርቡት ካርትሬጆች በኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ ወይም በዓለም አቀፍ የደረጃዎች ድርጅት (ISO) ደረጃ የወጣላቸው መሆን አለባቸው፡፡

7. <u>**ዝርዝር መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**</u>

የፌደራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ፈቃድ የተሰጣቸው አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ሊከተሉት ስለሚገባ አሠራር ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

8. <u>**መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**</u>

ይህ መመሪያ ከ ___________ ቀን ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

አዲስ አበባ ጥቅምት 18 ቀን 2006

ዓ.ም

ሱፍያን አህመድ
የገንዘና ኢኮኖሚ ልማት
ሚኒስትር

**የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር**

**Ministry of Finance and Economic Development**

# ማስታወሻ

# MEMO

**ለ :** ክቡር ሚኒስትር

*To:*

**ከ:** ሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

*From :*

**ቀን:** 13/02/2006

*Date:*

**ጉዳዩ፡ – <u>የመሚያ ረቂቅ ስለማቅረብ፣</u>**

የአገልግሎት ጠቀሜታ ጨርሰው በመንግሥት መ/ቤቶች የሚገኙ የቶነር ካርትሬጆች በፌደራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ለተደራጁ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት እንዲሰጡና ሙሉ ጥቅም ላይ የሚዋል ሥራ እንዲሠራ ለማድረግ ለሁሉም የፌደራል መንግሥት መ/ቤቶች አንድ መመሪያ ተቀርጾ እንዲተላለፍላቸው የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በቁጥር መግኤ/72/1/1/544 በ27/1/2006 በተጻፈ ደብደቤ ጠይቀዋል፡፡

በዚሁ መሰረት በክፍላችን የተዘጋጀውን አንድ ገጽ መመሪያ በዚህ ማስታወሻ አባሪነት አቅርበናል፡፡

ከማክበር ሠላምታ ጋር

**በትምህርት ሚኒስቴር በተዘጋጀው የጋራ ቅጥር መመሪያ ረቂቅ ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎችን ስለማቅረብ ፣**

የትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን የባለሞያ እጥረት ለመቅረፍ እንዲረዳ በሚል ባዘጋጀውን የጋራ ቅጥር አፈጻጸም መመሪያ ላይ አስተያየት እንዲሰጠው በ30/04/06 በቁጥር 7/ጡ-259/1220/06 በተፃፈ ደብዳቤ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት የሚከተለውን አስተያየት አቅርበናል፡፡

## 1. አንቀጽ 4 – ዓላማ

1.1. በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 34 ሁለቱ ዓላማዎች "ወይም" በሚል ቃል የተጣመሩ በመሆኑ "እና/ወይም" የሚለው ማሠሪያ ከአዋጁ ጋር የሚጣጣም ባለመሆኑ ሊስተካከል ይገባል፡፡

1.2. በተራ ቁጥር 4.2 በአዋጁ የተደነገገውን የሚደግም በመሆኑ በዚህ ፈንታ መመሪያው ተቋማት ለሚያወጡት ዝርዝር መመሪያና የሥነ-ሥርዓት ደንብ እንደመነሻ ሆኖ የሚያገለግል መሆኑ ቢገለጽ የተሻለ ነው፡፡

## 2. አንቀጽ 5 – መርሆዎች

2.1. አንቀጹ የመመሪያውን መርሆዎች ለማስተዋወቅ የተደነገገ ይበል እንጂ በመርሆነት ከሚታወቁ በጣም የራቁ ጉዳዮችን ተገቢነት በሌለው መንገድ አዘበራርቆ ያካተተ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 ማስታወቂያ ስለማውጣት፣ ስለወድድር እና ስለቅጥር አፈጻጸም የተደነገጉት "የቅጥር ሥርዓት" የሚል ወይም ተመጣጣኝ ርዕስ በሚሰጠው አንድ አንቀጽ ሊገቡ ይገባ እንደሆነ እንጂ መርሆ በሚለው ወስጥ ሊካተቱ የሚገባ አይደለም፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በንዑስ አንቀጽ 6፣ 8 እና 9 ያሉት ስለቅሬታ አቀራረብ የተደነገጉት በመሠረቱ ያለመግባባትን የመፍታት ጠባይ ያላቸው ድንጋጌዎች ስለሆኑና ከመርሆ ጋር የማይገናኙ በመሆናቸው ከአንቀጽ 5 እንዲወጡ ተደርጎ " ያለመግባባትን ስለመፍታት" የሚል አንድ አንቀጽ ሊዘጋጅላቸው ይገባል፡፡

2.2. በንዑስ አንቀጽ 2 ላይ ከ"ሀ" እስከ "ሠ" የጋራ ቅጥር በሚፈፀምበት ጊዜ በቅደም ተከተል ሥራ ላይ ሊወሉ የሚገባ አማራጮች መሆናቸው ተገልጿል፡፡ ነገር ግን ረዳት ምሩቃንን

አግባብነት ባለው የአዋጁ ድንጋጌ መሠረት መቅጠር "ከጋራ ቅጥር" ዓላማ ጋር የሚሄድ ስለሆነ ሊታይ ይገባል፡፡

2.3. በተራ ቁጥር 4 የሠፈረው አገለላጽ ግልጽ ስላልሆነ "የጋራ ቅጥር በባለሞያውና በአሠሪው መካከል በሚደረስ ስምምነት መሠረት ይፈፀማል" በሚል ቢስተካከል፡፡

2.4. በተራ ቁጥር 6 የተመለከተው ያለመግባባት መንስኤው "የጋራ ቅጥር ውል ስምምነት" አተረጓጐም ሊሆን ስለሚችል ስምምነቱ ያለመግባባትን እንደሚፈታ ማመልከቱ ተገቢ አይሆንም፡ በመሆኑም የቅጥሩ ውል አፈፃፀም ተቋሙ ባወጣው የወስጥ አሠራርና ደንብና ሥርዓት እንዲሁም በሁለቱ ወገኖች መካከል በተፈረመ የጋራ ቅጥር ውል የሚገዛ መሆኑ ቢመለከት የተሻለ ይሆናል፡፡

25. ተራ ቁጥር 7 አስፈላጊ ካለመሆኑም በላይ አሠሪ የተዘረዘሩት ኃላፊነቶች የሌሉበት መሆኑ ግልጽ ስለሆነ ማፃፉ ከማደናገር በስተቀር ጠቀሜታ የለውም፡፡

2.6. በተራ ቁጥር 8 የተመለከተው ያለመግባባትን አፈታት የማገልጽ ስለሆነ ከላይ እንደተገለፀው ራሱን በቻለ ያለመግባባት የሚፈታበትን ሁኔታ በሚመለከት አንቀጽ ስር ቢቀመጥ የተሻለ ይሆናል፡፡

2.7 በተራ ቁጥር 9 የተመለከተው የጋራ ቅጥር ባለሞያው አቤቱታ ካቀረበበት ጊዜ ጀምሮ በ93 ቀናት ወስጥ ቦርድ ወሳኔ ማስጠት እንዳለበት ለማመልከት የተቀማጠ ቢሆንም፡ አቀራረፁ ግልጽ ስላልሆነ እንደገና ሊታይ ይገባል፡፡

## 3. <u>አንቀጽ 6 የማስፈጸም ሥልጣን</u>

በተራ ቁጥር 6.3 ስለገቢ ግብር የተመለከተው ሀረግ ፈቃዱ ባልተገኘበት ሁኔታ "ፈቃዱ ሲገኝ" ተብሎ በመመሪያ ማስቀመጥ ተገቢ ስላልሆነ ተራ ቁጥሩ በሙሉ ሊወጣ ይገባል፡፡

## 4. <u>አንቀጽ 9 - የጋራ ቅጥር ባለሞያ መብቶች</u>

በተራ ቁጥር 9(2) በስህተት ለተከፈለ ገንዘብ ከፋዩ አንጂ ተቀባዩ ተጠያቂነት እንደሚኖረው የተመለከተው ፀንተው ከሚሠራባቸው ሕጎች ጋር የሚጣጣም ስላልሆነ ሊወጣ ይገባል፡፡

## 5. አንቀጽ 10 የደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞች አወሳሰን

በተራ ቁጥር 5 የተመለከተው በገቢ ግብር አዋጅ ገቢን ስለማጣመር ከተደነገገው ጋር የሚቃረን ስለሆነ ሊወጣ ይገባል፡፡

## 6. ማጠቃለያ

ከዚህ በላይ በአጭሩ ለማሳየት እንደተሞከረው መመሪያው የአቀራረፅና የይዘት ችግሮች ያሉበት በመሆኑ እነዚህ ስህተቶች በሚገባ ተመርምረው ማስተካከል ይገባቸዋል፡፡

ስለዚህ እነዚህ ነጥቦች ከግምት ወስጥ ገብተው የመመሪያው ረቂቅ እንደገና ቢታይ የተሻለ ስለሚሆን ይኸው ለጠየቂው ክፍል እንዲገለጽ ይህንን አስተያየት አቅርበናል፡፡

የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

Ministry of Finance and Economic Development

**ማስታወሻ**

# MEMO

**ለ፡ ክቡር ማግሥት ፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥር**
**ዘርፍ ሚኒስትር ደኤታ**

*To:*

**ከ፡ ህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት**

*From :*

**ቀን፡ 23/05/2006**

*Date:*

**ጉዳዩ፣ ከማግሥት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ ወደግል ድረጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ ገንዘብ በማስተላለፍ ስለቀረበው የወሳኔ ሃሣብ ይመለከታል**

በርዕሱ በተጠቀሰው ጉዳይ የቀረበወን የወሳኔ ሃሣብ ተመልክተን የሕግ አስተያየት እንድናቀርብ በታዘዘው መሠረት ቀጥሎ ያለወን አጠር ያለ አስተያየት እናቀርባል፡፡

1. የግል ድርጅቶች ሠራተኞች የጡረታ ፈንድ ከማግሥት አቻው የገንዘብ ድጋፍ የተደረገለት በወሳኔ ሃሣብ ወስጥ እንደተብራራው ፈንዱ አቅም ያላጎለበት በመሆኑና በተለይም ከማግሥት ደርጅቶች ወደ ግል ድርጅቶች የሚገጡ ሠራተኞች ይህንኑ መብታቸወን ይዘው የሚቀጠሩ በመሆናቸው እንደሆነ ተረድተናል፡፡

2. በማግሥት ድርጅት ማሥሪያ ቤቶች በተሰጠ አገልግሎት ወቅት የተከፈለ የጡረታ መዋጮ የሠራተኛወን አካሔድ ተከትሎ ወደ ግል ድርጅት የጡረታ ፈንድ ማስተላለፍ ተገቢ የሆነው አሠራር ቢሆንም ይህን ሚፈጸም ያልተቻለው በወሳኔ ሃሣብ ወስጥ እንደተጠቀሰው ሁሉ መዋጮው በግል ሂሣብ ያልተያዘ አብዛኛው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተሰበሰበ አንዳንዶቹም በፈረሱ ወይም ወደግል በተዛወሩ ድርጅቶች ለተፈጸመ አገልግሎት ወቅት ገቢ የተደረጉ በመሆኑ የመዋጮወን ሂሣብ ለይቶ ማስተላለፍ የሚቻል ያለመሆኑ ተጠቅሷል፡፡

3. ስለሆነም ሲሰበሰብ የቆየው የጡረታ መዋጮ ወደግሉ ፈንድ ሊዛወር ያልቻለው የተለየ ሕጋዊ ምክንያት ኖሮት ሳይሆን ለመተግበር አስቸጋሪ በመሆኑ ነው የሚለወን አቋም ማየት ይቻላል፡፡ ይህ አቋም ሲገፋበት የማግሥት ሠራተኞች የጡረታ ፈንድ ሕጋዊ

ግዴታወን ሳይወጣ የቀረና በዚሁ ማጠንም ሊበለጽግ የቻለ ሲሆን የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ በአንፃሩ ከማግሥታዊ አቻው በሕጋዊ ማንገድ ሊያገኝ ይገባ የነበረወን ገንዘብ ከአዋጅ ቁጥር

715/2003 አንቀጽ 15(3) ድንጋጌ ውጭ በሆነ የአሠራር ያለመሟላት ምክንያት ያለማገኘቱ የጎዳው መሆኑን ሚዳት ይችላል፡፡

ስለሆነም የቀረበው የወሳኔ ሃሣብ ይህንን ክፍተት መሙላትን ማሻ ያደረገና ሕጋዊና ተግባራዊ ምክንያት ያለው ስለሆነ ቢተገበር እያልን አስተያየታችንን እናጠቃልላለን፡፡

ከማክበር ሠላምታ ጋር

የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

Ministry of Finance and Economic Development

# ማስታወሻ

# MEMO

ለ፡ ክቡር ማኅበራዊ ፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥር
ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ

*To:*

ከ፡ **ሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት**

*From :*

**ቀን፡** 26/05/2006

*Date:*

ጉዳዩ፡- <u>በትምህርት ሚኒስቴር በተዘጋጀው የጋራ ቅጥር መመሪያ ረቂቅ ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎችን ስለማቅረብ</u>፣

የትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን የባለሞያ እጥረት ለመቅረፍ እንዲረዳ በሚል ባዘጋጀውን የጋራ ቅጥር አፈጻጸም መመሪያ ላይ አስተያየት እንዲሰጠው በ30/04/06 በቁጥር 7/ጡ-259/1220/06 በተፃፈ ደብዳቤ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት የሚከተለውን አስተያየት አቅርበናል፡፡

## 7. <u>አንቀጽ 4 - ዓላማ</u>

1.1. በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 34 ሁለቱ ዓላማዎች "ወይም" በሚል ቃል የተጣመሩ በመሆኑ "እና/ወይም" የሚለው ማሥሪያ ከአዋጁ ጋር የሚገጥም ባለመሆኑ ሊስተካከል ይገባል፡፡

1.2. በተራ ቁጥር 4.2 በአዋጁ የተደነገገወን የሚደግም በመሆኑ በዚህ ፈንታ መመሪያው ተቋማት ለማውጣት ዝርዝር መመሪያና የሥነ-ሥርዓት ደንብ እንደመነሻ ሆኖ የሚያገለግል መሆኑ ቢገለጽ የተሻለ ነው፡፡

## 8. <u>አንቀጽ 5 - መርሆዎች</u>

2.1. አንቀጹ የመመሪያውን መርሆዎች ለማስተዋወቅ የተደነገገ ይበል እንጂ በመርሆነት ከሚታወቁ በጣም የራቁ ጉዳዮችን ተገቢነት በሌለው መንገድ አዘበራርቆ ያካተተ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 ማስታወቂያ ስለማውጣት፣ ስለወድድር እና ስለቅጥር አፈጻጸም የተደነገጉት "የቅጥር ሥርዓት" የሚል ወይም ተመጣጣኝ ርዕስ በሚሰጠው አንድ አንቀጽ ሊገቡ ይገባ እንደሆነ እንጂ መርሆ በሚለው ወስጥ ሊካተቱ የሚገባ አይደለም፡

ከዚህም በተጨማሪ በንዐስ አንቀጽ 6፣8 እና 9 ያሉት ስለቅሬታ አቀራረብ የተደነገጉት በመሠረቱ ያለመግባባትን የመፍታት ጠባይ ያላቸው ድንጋጌዎች ስለሆኑና ከመርሆ ጋር

የሚገናኙ በመሆናቸው ከአንቀጽ 5 እንዲወጡ ተደርጎ " ያለመግባባትን ስለመፍታት" የሚል አንድ አንቀጽ ሊዘጋጅላቸው ይገባል፡፡

2.2. በንዑስ አንቀጽ 2 ላይ ከ"ሀ" እስከ "ሠ" የጋራ ቅጥር በሚፈፀምበት ጊዜ በቅደም ተከተል ሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባ አሠራሮች መሆናቸው ተገልጿል፡፡ ነገር ግን ረዳት ምጉቃንን አግባብነት ባለው የአዋጁ ድንጋጌ መሠረት መቅጠር "ከጋራ ቅጥር" ዓላማ ጋር የሚሄድ ስለሆነ ሊታይ ይገባል፡፡

2.3. በተራ ቁጥር 4 የሠፈረው አገለላጽ ግልጽ ስላልሆነ "የጋራ ቅጥር በባለሞያውና በአሠሪው መካከል በሚደረስ ስምምነት መሠረት ይፈፀማል" በሚል ቢስተካከል፡፡

2.4. በተራ ቁጥር 6 የተመለከተው ያለመግባባት መንስኤው "የጋራ ቅጥር ውል ስምምነት" አተረጓጐም ሊሆን ስለሚችል ስምምነቱ ያለመግባባትን እንደሚፈታ ማመልከቱ ተገቢ አይሆንም፡ በመሆኑም የቅጥሩ ውል አፈፃፀም ተቋሙ ባወጣው የወስጥ አሠራርና ደንብና ሥርዓት እንዲሁም በሁለቱ ወገኖች መካከል በተፈረመ የጋራ ቅጥር ውል የሚዳኙ መሆኑ ቢመለከት የተሻለ ይሆናል፡፡

25. ተራ ቁጥር 7 አስፈላጊ ካለመሆኑም በላይ አሠሪ የተዘረዘሩት ኃላፊነቶች የሌሉበት መሆኑ ግልጽ ስለሆነ መፃፉ ከሚያደናግር በስተቀር ጠቀሜታ የለውም፡፡

2.6. በተራ ቁጥር 8 የተመለከተው ያለመግባባትን አፈታት የሚገልጽ ስለሆነ ከላይ እንደተገለፀው ራሱን በቻለ ያለመግባባት የሚፈታበትን ሁኔታ በሚያመለክት አንቀጽ ስር ቢቀመጥ የተሻለ ይሆናል፡፡

2.7 በተራ ቁጥር 9 የተመለከተው የጋራ ቅጥር ባለሞያው አቤቱታ ካቀረበበት ጊዜ ጀምሮ በ93 ቀናት ወስጥ ቦርድ ወሳኔ ማስጠት እንዳለበት ለማመልከት የተቀመጠ ቢሆንም፡ አቀራረፁ ግልጽ ስላልሆነ እንደገና ሊታይ ይገባል፡፡

9. <u>አንቀጽ 6 የማስፈጸም ሥልጣን</u>

በተራ ቁጥር 6.2 ስለገቢ ግብር የተመለከተው ሀረግ ፈቃዱ ባልተገኘበት ሁኔታ "ፈቃዱ ሲገኝ" ተብሎ በመሟያ ማስቀመጥ ተገቢ ስላልሆነ ተራ ቁጥሩ በሙሉ ሊወጣ ይገባል፡፡

## 10. አንቀጽ 9 – የጋራ ቅጥር ባለሞያ መብቶች

በተራ ቁጥር 9(2) በስህተት ለተከፈለ ገንዘብ ከፋዩ አንጂ ተቀባዩ ተጠያቂነት እንደሚኖረው የተመለከተው ፀንተው ከሚሠራባቸው ሕጎች ጋር የሚጣጣም ስላልሆነ ሊወጣ ይገባል፡፡

## 11. አንቀጽ 10 የደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞች አወሳሰን

በተራ ቁጥር 5 የተመለከተው በገቢ ግብር አዋጅ ገቢን ስለማጣመር ከተደነገገው ጋር የሚቃረን ስለሆነ ሊወጣ ይገባል፡፡

## 12. ማጠቃለያ

ከዚህ በላይ በአጭሩ ለማየት እንደተሞከረው መመሪያው የአቀራረፅና የይዘት ችግሮች ያሉበት በመሆኑ እነዚህ ስህተቶች በሚገባ ተመርምረው ማስተካከል ይገባቸዋል፡፡

ስለዚህ እነዚህ ነጥቦች ከግምት ወስጥ ገብተው የመመሪያው ረቂቅ እንደገና ቢታይ የተሻለ ስለሚሆን ይኸው ለጠያቂው ክፍል እንዲገለጽ ይህንን አስተያየት አቅርበናል፡፡

ከማክበር ሠላምታ

ጋር

# የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

# Ministry of Finance and Economic Development

## ማስታወሻ

## MEMO

ለ :      አቶ ገላነህ አንጋሣ

*To:*   የክቡር ሚኒስትሩ ጽ/ቤት ኃላፊና አማካሪ

**ከ:**      **ሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት**

*From :*

**ቀን:**     15/05/2006

*Date:*

**ጉዳዩ፡ -   <u>ኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የጠየቀውን የሕግ ምክር ይመለከታል፣</u>**

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የማስታወቂያ ሽያጭ ሠራተኞችን በኮሚሽን ክፍያ ሥርዓት ለማሠራትና የትራንስፖርት አገልግሎትን የሚዟካ የማዘዋወሪያ አበል ለመክፈል ያደረገውን ጥናት በማያያዝ በጉዳዩ ላይ

የሕግ አስተያየት እንዲሰጠው በቁጥር መ72/3/256 ታህሳስ 15 ቀን 2006 ዓ.ም. በተጻፈ የጠየቀው ተሚቶልን በዝርዝር ተመልከተነዋል፡፡

ድርጅቱ የሚተዳደረው በራሱ ገቢ ሲሆን በጥናቱ እንደተጠቀሰውም የገቢውን 70 በመቶ የሚያገኘው ከዚሁ ከማስታወቂያ ሥራዎቹ ነው፡፡ ከመንግሥት የበጀት ድጋፍ እንደሚደረግለት በድርጅቱ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 113/87 እና 75/1989 (እንደተሻሻለው) በአንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1 በፊደል (ሀ) ላይ የተደነገገ ቢሆንም ድርጅቱ በደብዳቤው ላይ በተለይ ከ2003 ጀምሮ የበጀት ድጋፍ ተደርጉለት እንደማያውቅ ገልጿል፡፡ በዚሁ ጥናት ላይ ድርጅቱ ያጋጠመውን የገንዘብ ችግር ለመቅረፍና በማስታወቂያው ኢንዱስትሪ ወስጥ ተወዳዳሪ ሆኖ ለማዘለቅ የኮሚሽን የክፍያ ሥርዓት ለማዘርጋት ማቀዱንና አሁን ያለውን የማስታወቂያ ሥራን ቁርጥ ደመወዝ በሚከፈላቸው ሠራተኞች ማከራት ያስከተለውን ችግሮች በሚሣከት 11 ነጥቦችን ያቀረበ ሲሆን የትራንስፖርት አገልግሎትን በማዘዋወሪያ አበል ቢተካ ወጪን ከመቀነስ አኳያ የሚደረስባቸውን ወጠቶችም ጠቅሷል፡፡

በመንግሥት አስተዳደር ሠራተኞች የልዩ ልዩ አባሎች ክፍያ መመሪያ ቁጥር 1/መ58/31 መሠረት የማዘዋወሪያ (የትራንስፖርት) አበል የመንግሥትን ሥራ ለማከናወን የትራንስፖርት አገልግሎትን በመተካት የሚደረግ ክፍያ ሲሆን ይህ አበል ማጡኑ ከብር 800 በላይ ሲሆን የትራንስፖርት አበል ታክስ የሚከፈልበት መሆኑ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን መመሪያ የተደነገገ ስለሆነ ይህን መመሪያ በማለፍ የድርጅቱ የሽያጭ ሠራተኞች የትራንስፖርት አበል ከብር 800 በላይ ሲሆን ከታክስ ውጭ ሊደረግ የሚችልበት ሕጋዊ አሠራር የለም፡፡

የጥያቄው ሁለተኛና ዋነኛ ነጥብ የሆነውን የኮሚሽን ሽያጭ ክፍያም እንደዚሁ ጉልህ የሕግ ማሻሻያ የሚጠይቅና የመ/ቤቱ አደረጃጀትና ተጠሪነት አሁን ባለበት ሁኔታ ሊተገበር የሚችል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በዚህም መሠረት አሁን እየተጠየቀ ያለው የኮሚሽን ሽያጭ አሠራር የንግድ ሥራ ጠባይ ባላቸውና በመንግሥት የልማት ድርጅት ወስጥ የሚተገበር እንጂ ተጠሪነታቸው ለተወካዮች ምክር ቤት ወይም ለሚኒስቴር መ/ቤቶችና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ወ.ዘ.ተ. በሆነ መዋቅር ለሚተዳደሩ የባለሥልጣኑን መ/ቤቶች ኤጀንሲዎችና ድርጅቶች ወስጥ የሚከራበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በዚህም መሠረት ሠራተኞቹ በአዋጅ የትርጉማ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የመንግሥት ሠራተኞች ሲሆኑ ድርጅቱም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌዴራል የመንግሥት መ/ቤቶች ዝርዝር ወስጥ የሚገኝ የፌዴራል መንግሥት ተቋም ነው፡፡

ስለሆነም የመንግሥት ሠራተኞች የሆኑት የድርጅቱ ሠራተኞች ከሌሎች አቻ ተቋማት ሠራተኞች በተለየ ሜልኩ በኮሚሽን ክፍያ የሚከፍሉበት ሕጋዊ ምክንያት ባለመኖሩ፣ በተመሳሳይ የሥራ ሁኔታ ላይ ከተሰማሩ የመንግሥት መ/ቤቶች ማስል ጥያቄ እንዲቀርብ ቀደምትነት የሚፈጥር መሆኑ ስለሚገመት የድርጅቱ አቋም በመንግሥት መ/ቤትነት እስከቀጠለ ድረስ ለሠራተኛው የሚከፈለው በፌዴራል የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 በአንቀጽ 8 ላይ የተመለከተው ወርሃዊ ደመወዝ ብቻ በመሆኑ ጥያቄውን መቀበል የሚቻል

ማሆኑን እየገለጽን ጠቅላላው በመ/ቤቱ የቀረበው ጥናትና ጥያቄ በዚሁ አግባብ ምላሽ ቢሰጠው እያልን አስተያየታችንን እናጠቃልላለን፡፡

ከማክበር ሠላምታ

ጋር

# የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

# Ministry of Finance and Economic Development

## ማስታወሻ

## MEMO

**ለ:** **ትሬዠሪ ዳይሬክቶሬት**

*To:*

**ከ፡** **ሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት**

*From :*

**ቀን፡** **24/04/2006**

*Date:*

ጉዳዩ፡ - **<u>ከትራንስፖርት ሚኒስቴር ስለቀረበው የባህር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ አገልግሎት ድርጅትን ካፒታል የማሳደግ ጥያቄ ይመለከታል፣</u>**

በርዕሱ በተጠቀሰው ጉዳይ ድርጅቱ የተፈቀደ ካፒታሉን ለማሳደግ በእጁ የሚገኘውን የተጠራቀመ የመንግሥት የትርፍ ድርሻን ለካፒታል ማሳደጊያ እንዲሆን ለማስፈቀድ ያቀረበውን ጥያቄ በመደገፍ የትራንስፖርት ሚኒስቴር በ03/01/2006 በቁጥር 16፡2/2 የጻፈውን ደብዳቤና አባሪዎች በማያያዝ ታህሳስ 34 ቀን 2006 የላካችሁልን የውስጥ ማስታወሻ ተመልክተናል፡፡

ድርጅቱ ያቀረበውና በተቆጣጣሪው የሚኒስቴር መ/ቤት የተደገፈው የካፒታል ማሳደግ ጥያቄ ከአንዳንድ ታሳቢዎች አኳያ ታይተዋል፡፡

1ኛ. በማቋቋሚያው ሕግ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 255/2004 ላይ እንደተጠቀሰው ኮርፖሬሽኑ ሶስት ድርጅቶችን ያጠቃለለ ግዙፍ መዋቅር የተቋቋመና የካፒታል አቅም የሚጠይቁ ተግባራት የሚከናወን ተልዕኮ ያለው መሆኑ ይታወቃል፡፡ እነዚህ እንደ ደረቅ ወደቦች ግንባታና ማስፋፋት፣ የክሬኖችና የሞልቲ ሞዳል ሥርዓቱን ለማጠናከር የሚደረጉ የIT እና ሌሎች ግዢዎች ታሳቢ ያደረገ የ3 ቢሊዮን 760 ሚሊዮን ብር የተፈቀደ ካፒታል

ቢያዝለትም ከዚህ ወስጥ የተከፈለ ካፒታሉ 940 ሚሊዮን ብር መሆኑ የፋይናንስ አቅሙን የሚፈትን እንደሆነ ማገመት ስለሚቻል ጥያቄው የሚጠበቅ ነው፡፡

2ኛ. አንድ የንግድ ድርጅት ትርፉን ለካፒታል ማሳደጊያነትም ሊጠቀምበት እንደሚችል የሚታወቅ ሲሆን ኮርፖሬሽኑ ያቀረበው ጥያቄ ካፒታል ለማሳደግ በሚል ቢሆንም ጉዳዩ ይህን የሚያመለክት አልመሰለንም፡፡ የዚህም ዋነኛው ምክንያት ካፒታል ለማሳደግ ለሚቀርብ ጥያቄ የድርጅቱ የተፈረመ (የተፈቀደ)ካፒታል ተጠቃልሎ መከፈሉ ሕጋዊ ቅድመ ሁኔታ በመሆኑ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በኮርፖሬሽኑ የተፈቀደ ካፒታል እና የተከፈለ ካፒታል መካከል የብር 2.1 ቢሊዮን ልዩነት ስለሚታይ የኮርፖሬሽኑ የተፈቀደ ካፒታሉ ተጠቃልሎ ያልተከፈለ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ስለሆነም ያልተከፈለ ካፒታል ባለበት ወይም ይህ ክፍተት ባለበት ሁኔታ ካፒታል ለማሳደግ አይቻልም፡፡

ስለሆነም የመ/ቤቱ ጥያቄ የትርፍ ድርሻን (የመንግሥት የትርፍ ድርሻን) ወደተከፈለ ካፒታል የማዛወር ሊሆን ስለሚችል ጥያቄውን ከዚህ አቅጣጫ መመልከት አስፈልጓል፡፡

3ኛ. በዚህም መሠረት ኮርፖሬሽኑ እንደሚታወቀው ሁሉ ሥራውን የሚያካሂደው በተፈቀደ ካፒታሉ ሣይሆን በተከፈለለትና በእጁ በሚገኘው ካፒታል በመሆኑ ካፒታሉን መክፈል የኮርፖሬሽኑን የፋይናንስ አቅም የሚያጠናክርና መንግሥት ለይቶ የሰጠውን ተግባራት ለሚፈጸም የሚያግዘው ነው፡፡ ኮርፖሬሽኑ የሚያካሂዳቸው ተግባራት ከአገሪቱ ወጪና ገቢ ንግድ ጋር በቀጥታ የተያያዙና እነዚህኑ እንቅስቃሴዎች የሚደግፉ መሆናቸው ሲታሰብ ለኮርፖሬሽኑ የሚደረገው እገዛ ያለውን ዘላቂ ኤኮኖሚያዊ አንድምታ ሚረዳት ይቻላል፡፡ ኮርፖሬሽኑ የተሰጡትን ተግባራት ባሳካ ማጠን የአገሪቱን የሎጂስቲክስ አቅም የሚያጎለብቱ በመሆናቸው አገራዊ ጠቀሜታ ያለው ተግባር እንደሚሆን ይታሰባል፡፡

4ኛ. በሌላ በኩል በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/84 እንደተደነገገው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በየዓመቱ ከሚያገኙት ትርፍ ወስጥ የመንግሥትን የትርፍ ድርሻ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ገቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም በየዓመቱ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚፀድቀው የገቢ በጀት የፌደራል መንግሥት ገቢ ሆኖ ከሚወሰነው አንዱ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የትርፍ ድርሻ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ከባህር ትራንስፖርትና

ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት የሚገኘው የትርፍ ድርሻ በ2006 የበጀት አዋጅ በገቢ በጀትነት የታወጀ ከሆነ የድርጅቱን የተፈቀደ ካፒታል ለማሟላት እንዲውል ማድረግ አይቻልም፡፡

ለወደፊትም ቢሆን ከድርጅቱ የሚገኘው የትርፍ ድርሻ የመንግሥትን የወጪ በጀት ለማሟላት ወይስ የድርጅቱን የተፈቀደ ካፒታል ለማሟላት ይዋል? የሚለው የመንግሥትን የፍላጎት ቅደም ተከተል (Priority) ተከትሎ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል፡፡

ስለዚህ በጉዳዩ ላይ ያለን አስተያየት ከዚህ በላይ የተማለከተው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ

ጋር

# ማስታወሻ
# MEMO

**ለ:** ክቡር ሚኒስትር

*To:*

**ከ:** **ሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት**

*From :*

**ቀን:** 13/03/2006

*Date:*

**ጉዳዩ፡ - <u>ከኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የቀረበውን የተሽከርካሪዎች ማለዋወጫዎችና የመገናኛ መሣሪያዎች ከቀረጥ ነፃ የማስገባት ጥያቄ ይመለከታል</u>፣**

የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ከመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ የገዛቸውን አምስት ኮሮላ ሴዳን ተሽከርካሪዎች፣ ማለዋወጫዎቻቸውንና የመገናኛ መሣሪያዎች ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡለት በማጠየቅ በቁጥር 2/ፌፖኮ17/6/15 በ26/2/2006 በተጻፈ ደብዳቤ ባቀረበው ጥያቄ ላይ አስተያየት እንዲሰጥበት በታዘዘው መሠረት ተከታዩ ቀርቧል፡፡

በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለማስጠት እንዲረዳን ከኮሚሽኑ የተለያዩ ሰነዶችና ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲቀርብልን አድርገን በዝርዝር እንደተመለከትነው ፡-

1. ተሽከርካሪዎቹ፣ ማለዋወጫ የመገናኛ መሣሪዎቹ የተገዙት ከመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት ለኮሚሽኑ በተሰጠ የብር 13,500.000 (አስራ ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) ድጋፍ ሲሆን፣ የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤትም የተጠቀሰውን ገንዘብ ኮሚሽኑ ለትራፊክ ደህንነት እንቅስቃሴው እንዲያውለው የታቀደ በመሆኑ ተሽከርካሪዎቹ የተለያዩ የራዳር፣ የጂፒኤስ እና ሌሎች የቁጥጥር መሣሪያዎች የተገጠሙላቸውና ለዚሁ ተግባር እንዲውሉ የተዘጋጁ መሆኑን ከተያያዙት ሰነዶች ተገንዝበናል፡፡

2. ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ (ለ) በተራ ቁጥር 8 በተለይ ለመከላከያ ተግባር የሚውሉ ተሽከርካሪዎችና የመገናኛ መሣሪያዎች ከቀረጥ ነፃ የመግባት መብት የፌደራልና የክልል ፖሊስንም ይመለከት እንደሆነ ቀደም ሲል ተጠይቆ ሁለቱም ተቋማት ተጠቃሚ የሚሆኑባቸው ዕቃዎች ተለይተው የተገለጹ ሲሆን በመመሪያው ቁጥር 2 ንዑስ ቁጥር 2.7 " ሌሎች

ተሽከርካሪዎች " የሚለው ቃል ግን አሻሚ ሆኖ ስለተገኘ እነዚህ ተሽከርካሪዎች ለአድማ ብተና የሚውሉትን ብቻ ማለት እንደሆነ በክፍላችን ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ እስካሁንም በዚሁ አግባብ እየተስተናገደ ይገኛል፡፡

ስለሆነም የተሽከርካሪዎቹ እና ማለዋወጫ መሣሪያዎቹ ከቀረጥ ነፃ ማግባት የህግ ድጋፍ የሌለው መሆኑን እየገለጽን አስተያየታችንን እናጠቃልላለን፡፡

ከማክበር ሠላምታ ጋር

# የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

# Ministry of Finance and Economic Development

# ማስታወሻ

Memo/Tr/TA

# MEMO

**ለ:** ክቡር ሚኒስትር

*To:*

**ከ: ሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት**

*From :*

**ቀን:** 05/03/2006

*Date:*

ጉዳዩ፡ - <u>በኢትዮጵያ የአሜሪካን ኤምባሲ ስለቀረበው የተ.እ.ታ ተመላሽ ይመለከታል፣</u>

በርዕሱ በተጠቀሰው ጉዳይ የሕግ አስተያየት እንዲቀርብ በታዘዘው መሠረት ተከታዩን አስተያየት አቅርበናል፡፡

1. በኢትዮጵያ የአሜሪካን ኤምባሲ እ.ኤ.አ. አክቶበር 29 ቀን 2013 ለክቡርነትዎ በጻፈው ደብዳቤ ላይ እንደጠቀሰው ወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ ፣ ሚሽን ፎር ኮሚቲ ደቨሎፐመንት ፕሮግራም እና ሜፍናይት ኤኮኖሚክ ደቨሎፐመንት አሶሽየትስ የተባሉ ሶስት መንግስታዊ ያልሆኑ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ለሚያካሄዱት የሕጻናት የጉልበት ብዝበዛን በማስወገድ ላይ ያተኮረ ፕሮጀክት ሥራ ከአሜሪካን መንግሥት የሥራ ሚኒስቴር ( Department of Labor) ባገኙት እርዳታ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግሥት የተለያዩ ፕሮጀክቶችን እያካሄዱ ስለመሆኑ ከተላከልን ሰነዶች ተመልክተናል፡፡

2. ኤምባሲው ያቀረበው ጥያቄ እነዚህ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች የሚያካሄዱት የሕፃናት የጉልበት ብዝበዛን የማስወገድ ሥራ በተለያዩ ፕሮጀክቶች የሚዙገበር ስለሆነና ለፕሮጀክቶቹ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ በተ.እ.ታ. ተመላሽ እንዲስተናገዱ እንዲፈቀድ የሚል ነው፡፡ እ.ኤ.አ. ኖቬምበር 19 ቀን 1992 በሁለቱ

መንግሥታት መካከል የተደረገው የቴክኒካዊ ተራድኦ ስምምነት በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በአሜሪካ መንግሥት ዕርዳታና ድጋፍ ለሚከሄዱ ፕሮጀክቶች ማካሄጃ ወደ አገር የሚገቡም ሆነ በአገር ውስጥ የሚገዙ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ከማንኛውም ዓይነት ታክስ ነፃ እንዲደረጉ ስምምነት ተደርጓል፡፡

3. ከፍ ሲል በተራ ቁጥር 1 ላይ የተጠቀሱት 3 ግብረ ሰናይ ድርጅቶች የሚያካሄዱት የሕፃናት የጉልበት ብዝበዛን በማስወገድ ላይ ያተኮረ ፕሮጀክት ከአሜሪካን መንግሥት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ የሚካሄድ በመሆኑና በተራ ቁጥር 2 በተጠቀሰው የሁለትዮሽ የቴክኒክና ተራድኦ ስምምነት ሽፋን የሚካተት ስለሆነ በስምምነቱ መሠረት ከተ.እ.ታ. ተመላሽ ነፃ መብት ቢሰጣቸው እያልን አስተያየታችንን እናጠቃልላለን፡፡

ከማክበር ሠላምታ

ጋር

## የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

## Ministry of Finance and Economic Development

## ማስታወሻ

Memo/Tr/TA

# MEMO

**ለ፡** ክቡር ሚኒስትር

*To:*

**ከ፡ ሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት**

*From :*

**ቀን፡** 13/02/2006

*Date:*

**ጉዳዩ፡ – <u>የመሚያ ረቂቅ ስለማቅረብ፣</u>**

የአገልግሎት ጠቀሜታ ጨርሰው በመንግሥት መ/ቤቶች የሚገኙ የቶነር ካርትሬጆች በፌደራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ለተደራጁ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት እንዲሰጡና ሚልሶ ጥቅም ላይ የማዋል ሥራ እንዲሠራ ለማድረግ ለሁሉም የፌደራል መንግሥት መ/ቤቶች አንድ መሚያ ተቀርጾ እንዲተላለፍላቸው የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በቁጥር መግኤ/72/1/1/544 በ27/1/2006 በተጻፈ ደብደቤ ጠይቀዋል፡፡

በዚሁ መሻሻ በክፍላችን የተዘጋጀውን አንድ ገጽ መሚያ በዚህ ማስታወሻ አባሪነት አቅርበናል፡፡

ከማክበር ሠላምታ ጋር